# የጆርጅ ጎዳናው ጄነር

## (JENNER OF GEORGE STREET)

http://www.personaltract.com

*የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ዘርን የሚዘራ ሰውን ትመስላለች ብሎ ኢየሱስ ተናግሯል። ይህ የፍራንክ ጀነር (Frank Jenner) እና እንዴት እግዚአብሔር በጆርጅ ስትሪት፣ ሲድኒ (George Street, Sydney) የኢየሱስን ወንጌል የምስራች በምድር (በዓለም ዙሪያ) ለማሰራጨት እንደተጠቀመበት የሚገልጽ አስደናቂ ታሪክ ነው። እግዚአብሔር ይባርክህ ደግሞም ለኢየሱስ ክርስቶስ ደማቅ እና የማያፍር ምስክር እንድትሆን ኃይልን ያስታጥቅህ። ይህ የፍራንክ ጀነር ታሪክ የተዘጋጀው በ www.personaltract.com ሲሆን "የጆርጅ ጎዳናው ጀነር" (Jenner of George Street") በዶ/ር ሬይመንድ ዊልሰን (Dr Raymond Wilson) ከተጻፈው መጽሐፍ ላይ የተመሰሠረተ ነው።*

### ፍራንክ ጄነር - የጆርጅ ጎዳናው ሰባኪ

### የጆርጅ ጎዳናው ጄነር



ይህ ታሪክ የጀመረው ከረዥም አመት በፊት በእንግሊዝ ቦርንመዝ (Bournemouth) ከተማ በባፕቲስት ቤተ ክርስትያን ውስጥ ነው። (ፓስተር፣ ካህን) መጋቢ ዶ/ር ፍራንሲስ ዲክሰን (Dr. Francis Dixon) አንድ ምሽት ላይ ፒተር የሚባልን ሰው ምስክርነት እንዲሰጥ ጥያቄ አቀረበለት።

ፒተርም ተነስቶ እንዲህ አለ "*እኔ የዳንኩት እንደዚህ ነው። በሮያል ኔቪ (ንጉሣዊ ባሕር ኃይል) ውስጥ ነበር የምሠራው እናም በሲድኒ አውስትራሊያ በጆርጅ ስትሪት (በጆርጅ ጎዳና) እያለፍኩ ሳለሁ ከየት ነው ሳይባል አንድ ሰው አጠገቤ መጥቶ '**ይቅርታ ወንድሜ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እችላለሁ? ጥያቄው እንደማያስቀይምህ ተስፋ አደርጋለሁ። እናም ዛሬ የምትሞት ቢሆን የዘላለምን ህይወት የት የምታሳልፍ ይመስልሃል? መጽሐፍ ቅዱስ በገነት ወይም በሲኦል ነው ሊሆን የሚችለው ይላል። እባክህን ልታስብበት ትችላለህ? አመሰግናለሁ። እግዚአብሔር ይባርክህ።**' ብሎኝ ሄደ። ጥያቄውን ከዚህ በፊት ተጠይቄ አላውቅም እናም ከአይምሮዬ ውስጥ ማውጣት አልቻልኩም። ወደ እንግሊዝ ተመለስኩኝ ከዛም ከአንድ ሰው ጋር ተገናኘው እሱም ወደ ሆነ ተልዕኮ ወሰደኝ እናም እዛው ነው ክርስትያን የሆንኩት*"።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በቦርንመዝ ባለው ተመሳሳይ ቤተ ክርስትያን የወጣቶች ስብሰባ ነበራቸው እናም ከጎብኚው ቡድን ኖውል የሚባል ሰው ምስክርነቱን እንዲህ ሲል ሰጠ ። "*እኔ ኢየሱስ ክርስቶስን ያወኩት እንደዚህ ነበረ። በሮያል ኔቪ  ውስጥ ነበር የምሰራው እናም መርከቤ ሲድኒ ላይ ቆማ ነበር። አንድ ምሽት በጆርጅ ስትሪት እያለፍኩ ሳለሁ ከየት ነው ሳይባል አንድ ሰው አጠገቤ መጥቶ '**አንተ ወጣት የምጠይቅህ ጥያቄ አለኝ። ዛሬ ብትሞት የት የምትሄድ ይመስልሃል? ገነት ወይስ ሲኦል? ጥያቄውን ላለመመለስ እንዳትሞክር፡ ከሁለቱ አንዱ ነው መሆን ያለበት።**' አለኝ። የተናገረኝ ነገር ለብዙ ወራት ከነከነኝ ከዛም ክርስትያን ሰው ፈለኩኝ እሱም ረዳኝና ህይወቴን ለክርስቶስ ሰጠሁ።*"

አሁን ኢንግላንድ ያለው የባፕቲስቱ መጋቢ ጥያቄ ተፈጥሮበታል! ብዙም ሳይቆይ በደቡብ አውስትራሊያ በምትገኝ አዴላይድ (Adelaide) በምትባል ከተማ እየሰበከ ሳለ ነበር የፒተርንና የኖውልስን በጆርጅ

ስትሪት ካለው ሰው ጋር በተለያየ ጊዜ የተገጣጠሙብትን ታሪክ ሊነግራቸው የወሰነው። እንደነገራቸው፤ አንድ ሰው በደስታ ዘሎ ተነሳና እንዲህ አለ "*እኔም ሌላው ነኝ፣እኔም ሌላው ነኝ። ክርስቶስን እንድቀበል የተጋበዝኩት በተመሳሳይ መንገድና በተመሳሳይ ጆርጅ ስትሪት ባለው ሰው ነው።*"

ይሄ ደግሞ ኮርፖራል ሙሬይ ዊልክስ (Corporal Murray Wilkes) ይባላል። በጆርጅ ስትሪት ባቡር ለመያዝ በችኮላ ሲሄድ ሳለ ነው ከበስተኋላው "***አንዴ ቆየኝ***" የሚል ድምጽ የሰማው ፤ ሙሬይም ቆመና ወደኋላ ዞረ። ከፊቱ ያለው እንግዳው ሰውም እንዲህ ሲል ጠየቀው "***ወታደር፣ ዛሬ የምትሞት ቢሆን የት የምትሄድ ይመስልሃል? ገነት ወይስ ሲኦል?***" "*ገነት እሄዳለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ*" ብሎ ሙሬይ መለሰለት። "***ተስፋ ማድረግ ብቻ በቂ አይደለም፤ ማወቅ ትችላለህ!***" አለው እንግዳው ሰውዬ።

የእንግዳው ሰው ጥያቄ የሙሬይን ህይወት ውስጣዊ ጥያቄ አጋለጠበት። በጥሩ ሁኔታ የሚኖር፣ ቤተ ክርስትያን የሚሄድ፣ ትዳር ያለው ሰው ቢሆንም ያመነበትን ነገር የማያደርግ ግብዝ እንደሆነ የሚያውቅና እስካሁን ድረስ የዘላለም ፈንታ ጥያቄ ያልቀረበለት ሰው ነው። ከሁለት ሳምንት በኋላ ሙሬይ በጦር ስፍራ (በወታደሮች ትልቅ ህንጻ ውስጥ) ተንበረከከና ሕይወቱን ለክርስቶስ ሰጠ።

ዶ/ር ፍራንሲስ ዲክሰን ጉዞውን ቀጥሏል እናም በፐርት (Perth) በመስበክ ላይ እያለ በድጋሚ እነዚህን ታሪኮች አካፈላቸው። በመቀጠል አንድ ወጣት ወደ እርሱ መጥቶ እርሱም እንዴት በኔቪ ውስጥ ሲሠራ እንደነበረና ጆርጅ ስትሪትን በመጎብኘት ላይ ሳለ ከእንግዳው ሰውዬ ጋር እንዴት እንደተገናኘና ከሚያሳምነው ጥያቄ በኋላ እንዴት ክርስትያን እንደሆነ ነገረው።

ዶ/ር ዲክሰን በመጨረሻ ሲድኒ ከደረሰ በኋላ ስለዚህ የከተማ ወንጌላዊ ተጨማሪ ነገር ማወቅ ፈለገና ለአንድ ክርስትያን ሠራተኛ ፤ "*በጆርጅ ስትሪት ያለው ሰው ማነው?*" አለው። "*በደንብ ነው የማውቀው፤ ስሙም ፍራንክ ጄነር ይባላል።*" ብሎ መለሰለት።

ፍራንሲስ ዲክሰን ወደ ትሁቷ ትንሽ ቤት ተወሰደና ከፍራንክ ጄነር ጋር ተዋወቀ። ፍራንሲስ የአራቱን ወጣት ወታደሮች ታሪክና እሱ በጠየቃቸው ቀላል ጥያቄ እንዴት ወደ ክርስቶስ እንደመጡ ሲያጫውተው፤ ፍራንክ ማንባት ጀመረ። "***ካናገርኳቸው ሰዎች መካከል ማንም ወደ ጌታ እንደመጣ ሰምቼ አላውቅም ነበር። ጥቂት ሰዎች በቅዳሜ ምሽት ምስክርነት ላይ ካናገርኳቸው በኋላ ወስነው ከዚያም እሁድ ጠዋት ለቁርስ እቤት መተው ነበር (አንዳንዴ 30 ሰዎች ከእኔ ጋር እቤት መጥተው ነበር) ነገር ግን ከዚያ በላይ አላውቅም ነበር።***"

ፍራንክ ይሄን ሥራ ለአስራ ስድስት ዓመታት ሲያከናውን፤ የመጨረሻውን ውጤት ሲሰማ የመጀመርያው ጊዜው ነበር። ለብዙ ዓመታት ምንም አይነት ውጤት ሳያይ ይህን ሥራ ሲሠራ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እንደዛ አይነት አድናቆትና ፍቅር ለማሳየት በደንብ ራሱን ሰጥቶ ነበር ማለት እችላለሁ።

በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ፍራንሲስ ዲክሰን በዓለም ዙርያ ሲሰብክ የፍራንክ ጄነርን ታሪክ አልፎ አልፎ ይናገር ነበር።

በእንግሊዝ – ኢቫንጄሊካል ስብሰባ ላይ ፓስተሮች (መጋቢዎች) ወደ እርሱ መጥተው በእንግዳው ሰውዬ አስደንጋጭ ጥያቄ እንዴት እንደተማረኩ ነግረውት ነበር።

በህንድ በነበረው የወንጌላውይን ስብሰባ ላይ አንድ ህንዳዊ በአንድ የሲድኒ ቀይታው በፍራንክ ጥያቄ እንዴት እንደተፈተነ እና ብዙም ሳይቆይ ክርስቶስን ተቀብሎ ወደ ክርስትያን አገልግሎት እንደገባ ነገረው።

በጃማይካ – የወንጌላውያን ስብሰባ ላይ ደግሞ ሁለት ወንጌላውያን ከፍራንክ ጄነር ምስክርነት በኋላ ወደ ኢየሱስ ከዓመታት በፊት እንደመጡ ሰማ።

በአሜሪካን – የባሕር ኃይል ቀሳውስት (naval chaplains') ስብሰባ ላይ ስለጆርጅ ስትሪቱ ሰውና ስለምስክርነቱ አካፈላቸው። አንድ ቄስ ተነስቶ እሱም በፍራንክ ጄነር ማራኪ ጥያቄ ምክንያት ወደ ክርስቶስ እንደመጣ አካፈላቸው።

በዚያች የአንድ መስመር ምስክርነት የስንት ሰዎች ህይወት እንደተነካ ለማወቅ አዳጋች ነው። ነገር ግን የፍራንክ ጄነር አስተዋጽኦ በቀላል ቁጥሮች ከሚገለጸው በላይ የሚለካው በዘለቄታዊነቱ ነው።

የፍራንክ እያንዳንዱ የእምነት ጉዞው ልክ እርሱ እንደነካቸው ሰዎች ህይወት አስደናቂ ነው። ፍራንክም "*ኢየሱስ ክርስቶስን ከማወቄ በፊት የአንድን መርከበኛ አስቀያሚ ህይወት ሁሉ እኖር ነበር ከዚያም የቁማር ሱሰኛ ሆንኩኝ። ከዚያም በ1937 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.) አዳኜን ለመጀመርያ ጊዜ አገኘሁትና ህይወቴ ተቀየረ። የቁማር ሱሴም ለዘላለም ከኔ ላይ ተወገደ።*" በማለት ተናገረ። በህይወቱ ሁለተኛ እድልን ስላገኘ ፤ እግዚአብሔርን በሙሉ አቅሙ ለማገልገል ቃል ገባ። "*አላማዬ በእያንዳንዱ ቀን ለ10 ሰዎች ስለኢየሱስ ክርስቶስ መናገር ነበር። ይሄንንም ለ28 ዓመታት የ"ፓርኪንሰንስ" (perkinsons) በሽታ እስኪበረታብኝ ድረስ ሳከናውን ነበር። በጦርነትና በሰላም በመልካምና በመጥፎ ጊዜያት ሁሉ ቃል የገባሁትን ሥራ እሠራ ነበር*" ብሎ ተናገረ። ፍራንክ በዛ ሁሉ ዓመታት ከመቶ ሺህ በላይ ሰዎች ጋር ተነጋግሯል ተብሎ ይገመታል። በትክክል ብዙ መጋቢዎች በህይወታቸው ሙሉ ሊያሳኩት ከሚችሉት በላይ ነው።

በቀጣዮቹ ዓመታት የፍራንክ ጤና እየባሰበት ሄደ፤ በመጨረሻ ቀናቶቹ ላይ እንዲህ በማለት ጸለየ፤ "***ጌታዬ ሆይ፥ እባክህን እሁድ ምሽት ላይ ወደ ቤቴ ውሰደኝ።***" የመጨረሻ ጥያቄውም ተፈቀደለት። እሁድ ምሽት ለእኩለ ሌሊት ግማሽ ሠዓት ሲቀረው ህይወቱ አለፈ። በሚቀጥለው ጠዋት የፀሐይ ጨረር በተከፈተው መስኮት ገብቶ በሚገባ በተጠቀመበት መጽሐፍ ቅዱስ ላይና እላዩ ላይ ባለችው ብቸኛ አበባ ላይ አረፈ።

ሲድኒ ካሉት ጥቂት የክርስትያን ሰዎች በስተቀር ፍራንክ ጄነርን የሚያውቅ ማንም አልነበረም። ነገር ግን እውነት እላቹሃለሁ ስሙ በገነት የሚታወቅ ነበረ። ገነት ታውቀው ነበረ እናም በክብር ወደ ቤቱ ሲሄድ ምን ዓይነት አቀባበል እንደተደረገለት ማሰብ ትችላላችሁ።

ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "*በሰዎች ፊት ስለእኔ ብትመሰክሩ እኔም በሰማያት በአባቴ ፊት እመሰክርላቹሃለሁ።*" (ማቴዎስ 10፡32) በግሌ የማምነው ኢየሱስ ክርስቶስ የፍራንክን ስም በተደጋጋሚ በገነት ለአባቱ እንደመሰከረለት ነው። (በተቃራኒው ደግሞ ኢየሱስ "በሰዎች ፊት ስለእኔ ባትመሰክሩ እኔም በሰማያት በአባቴ ፊት አልመሰክርላችሁም" ብሎ ተናግሯል። (ማቴዎስ 10፡33))

በእርግጥም በምድር ከመታወቅ በላይ በሰማይ ባለው አባታችን ፊት መታወቅ ይበልጣል ምክንያቱም ብድራታችን ያለው በዛ ነው።

በግሌ የፍራንክ ጄነር ፊት ወይም ደግሞ ታሪኩ ከጥቂት አንቀጾች በላይ በማናቸውም ታዋቂ የክርስትያን መጽሔቶች ላይ የታተመ አይመስለኝም። እግዚአብሔር ግን ይህን ኢየሱስን በጣም ያከበረውን ሰው አክብሮት ታሪኩን አስነገረለት።

እግዚአብሔር ይባርክህ ደግሞም ለ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ደማቅ እና የማያፍር ምስክር እንድትሆን ኃይልን ያስታጥቅህ።

## በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ቢኒያም ጌታቸው
Translated to Amharic by Biniyam Getachew, bgmanoftheyear@gmail.com